M● ST

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

# የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር
# ሀገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና
# የሽልማት መመሪያ

**570/2013**

ሚያዝያ 2008

አዲስ አበባ

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሀገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሽልማት መመሪያ ቁጥር 570/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "ሽልማት" ማለት በመንግስትና በግል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ ወይም ተቋም በላቀ የፈጠራ ስራቸው የሚሸለሙ አሰልጣኞችንና ሰልጣኞችን የሚያካትት የሜዳሊያ፣ የገንዘብ፣ የሰርተፍኬት እና ስልጠና ማበረታቻዎችን ይመለከታል፣
2. "የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ ወይም ተቋም" ማለት ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ አምስት የሚያሰለጥን በተለይም ቴክኖሎጂን በመረዳት፣ በማላመድ፣ በመቅዳትና በማሻሻል ትኩረት ሰጥቶ የሚያሰለጥን ተቋም ወይም ኮሌጅ ነው፣
3. "ጉድኝት ማዕከል" ማለት የተለያዩ ኮሌጆችን ወይም ተቋማትን በመረብ የሚያገናኝ፣ በሰው ሀይል እና በማቴሪያል የሚደጋገፉበት እንዲሁም የልምድ ልውውጣቸውን የሚያሳዩበት ማዕከል ነው፣
4. "የፈጠራ ስራ" ማለት አዳዲስ ሃሳቦችን በማመንጨት ወይም በምርት ሂደት ያለ ቴክኖሎጂን ወይም አሠራርን በማሻሻል ወይም በመቅዳት የተዘጋጀ ፕሮቶታይፕ ወይም ሥራ ላይ የሚውል ወይም የዋለ የሥራ ውጤት ነው፣
5. "ሠልጣኝ" ማለት በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ወይም ተቋም በመደበኛ መርሀ-ግብር ተመዝግቦ የሚሰለጥን ነው፣
6. "አሠልጣኝ" ማለት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ወይም ተቋም በሙሉ ጊዜ የሚያሰለጥን ባለሙያ ነው፣
7. "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፣
8. "ኤጀንሲ" ማለት በክልሎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች የሳይንስና ቴክኖሎጂ ነክ ስራዎችን ለመምራትና ለማስተባበር የተቋቋሙ አካላትን ይመለከታል፣

9. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለፀው ሴትንም ያካትታል፡፡

## 3. የመመሪያው ዓላማ

መመሪያው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. ወጣት ሰልጣኞች ወደ ፈጠራ ስራ ገብተው ለወደፊት ባለሀብቶች እና አዲስ ቴክኖሎጂ ፈጣሪዎች የሚሆኑበትን አቅም ለማስፋት፣
2. በፈጠራ ስራዎቻቸውና በክህሎታቸው አርአያ የሆኑ የቴክኖሎጂ ትምህርት አሰልጣኞችን ዕውቅና ለመስጠት፣
3. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍን ለማበረታታትና ሀገራዊ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ባህልን ለማዳበር፣
4. በንድፈ ሃሳብ የሚሰጠውን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናን ከተግባር ጋር በማስተሳሰር ቴክኖሎጂ መቅዳትን ለማበረታታት፣
5. የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴዎች በመላው ህብረተሰብ እንዲታወቁና ህዝባዊ መነሳሳትና የውድድርና የፈጠራ መንፈስን እንዲፈጠር ለማድረግ፡፡

## 4. የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ በዘጠኙ ብሔራዊ ክልሎችና በሁለቱ የከተማ መስተዳድሮች በሚገኙ የመንግስትና የግል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች ወይም ተቋማት በሚያሰለጥኑና በሚሰለጥኑ አሰልጣኞችና ሰልጣኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# <u>የተወዳዳሪዎች አግባብነት፣ መምረጫ መስፈርቶች እና የተሸላሚዎች አመራረጥ ሂደት</u>

## 5. የተወዳዳሪዎች አግባብነት

1. ሽልማቱ የሚያካትተው በመንግስትና በግል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማት ሙሉ ጊዜያቸውን በማሰልጠን የሚያገለግሉ ኢትዮጵያዊያን አሰልጣኞች፣ እንዲሁም በመደበኛ የትምህርት መርሀግብር በመሰልጠን ላይ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ሰልጣኞችን ነው፣

2. ሁሉም እጩ ተወዳዳሪዎች ለውድድር የሚቀርቡት በዋናነት በሠሩት ፕሮቶታይፖች ወይም ቴክኖሎጂዎች መሰረት ይሆናል፣
3. ለውድድር የሚቀርቡ የእጩ ተወዳዳሪዎች ፕሮቶታይፖች ወይም ቴክኖሎጂዎች በቡድን የተሰሩ ከሆነ በሚወክሉት አንድ ሰው ስም ለውድድር መቅረብ ይችላል፣
4. ለውድድር የሚቀርቡ ፕሮቶታይፖች ወይም ቴክኖሎጂዎች መረጃ በፎቶ ወይም በተንቀሳቃሽ ምስል ወይም በሲዲ ወይም በሰነድ የተደገፉና ተጨባጭ መሆን ይኖርባቸዋል፣
5. ከአንድ ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ወይም ተቋም የሚቀርቡ እጩ ተወዳዳሪዎች በተመሳሳይ ስራ ፕሮቶታይፖች ወይም ቴክኖሎጂዎች በተናጠል ለውድድር መቅረብ አይችሉም፣
6. ተወዳዳሪዎች የተሟላና በክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ ኃላፊው የተፈረመ የማመልከቻ ቅፅ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣
7. በሀገር አቀፍ የሳይንስ ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን በእጩነት የሚቀርቡት ተወዳዳሪ ሰልጣኞችና አሰልጣኞች ለክልልና ከተማ መስተዳድሩ በክልሉ ከሚገኙ ብቁ ተወዳዳሪዎች መካከል በዚህ መመሪያ መሰረት በተሰጠው ኮታ ልክ የተሻሉትን በመምረጥ ለሚኒስቴሩ የሚላኩ ይሆናል፣
8. ከዚህ ቀደም በሀገር አቀፍ ደረጃ የተሸለሙ ሰልጣኞችና አሰልጣኞች በተሸለሙበት ስራ ለውድድር መቅረብ አይችሉም፡፡

## 6. የመምረጫ መስፈርቶች

አሰልጣኞችና ሰልጣኞች በሚከተሉት መስፈርቶች ይመረጣሉ፡

1. እያንዳንዱ አሰልጣኝና ሰልጣኝ በዋነኝነት የሚመዘነው በተሰሩ ችግር ፈች ተስማሚና አዋጭ በሆኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ብቻ ነው፣
2. በውድድሩ ሴት ተወዳዳሪዎች ከወንዶች ጋር እኩል ነጥብ ካገኙ ሴት ተወዳዳሪዎች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡ እንዲሁም አካል ጉዳተኞች ከሌሎች ጋር ተወዳድረው በነጥብ እኩል ከሆኑ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፣
3. ተቋሙ ወይም ኮሌጁ እጩዎችን ለውድድር ሲያቀርብና ነጥብ ሲሰጥ በያንዳንዱ መስፈርት በተወዳዳሪው የተሰሩ ስራዎች በጽሁፍ በየመስፈርቱ ስር በመጻፍ ነጥብ ይሰጣቸዋል፡፡ እንዲሁም የስራዎቹ ደጋፊ ሰነዶችና ከተቋም የተሰጡ ማረጋገጫዎች ተያይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፣

4. ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ 1 ላይ በተዘረዘሩት መስፈርቶች መሠረት በዝርዝር ያልተገለጹ ስራዎች ዋጋ አይኖራቸውም፡፡

## 7. የተሸላሚዎች ድልድልና ብዛት

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲዎች ወይም ቢሮዎች በየዓመቱ ለሽልማት የሚያቀርቧቸው እጩ ተወዳዳሪዎች ብዛት በሚኒስቴሩ የሚገለጽ ይሆናል፡፡

## 8. የተሸላሚዎች አመራረጥ ሂደት

1. የአሰልጣኞችና ሰልጣኞች ምርጫ የሚጀምረው ከቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት ከሚገኙ ትምህርት ክፍሎች ነው፡፡ ከትምህርት ክፍሉ የተመረጡ እጩዎችን ተቋሙ በማወዳደር ወደ ክልሉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ ይልካል፣
2. እያንዳንዱ የክልልና ከተማ መስተዳድር ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ ከሚመለከታቸው ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ ወይም ኮሚሽን ጋር በመሆን እጩዎችን ይመርጣል፣
3. ኤጀንሲው የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ እጩ ተሸላሚ ሰልጣኞችና አሰልጣኞች ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ መሠረት በደረጃ በመለየት የስም ዝርዝር፣ የኮሚቴውን ቃለ ጉባኤና እጩው በየመስፈርቱ የሰራቸውን ስራዎችና ማስረጃዎችን በማያያዝ በማጠቃለያ አባሪ ቅጽ ሞልቶ ለሀገር አቀፍ የምርጦች ምርጥ ውድድር ለሚኒስቴሩ ይልካል፣
4. ሚኒስቴሩ ለሀገር አቀፍ ውድድር የቀረቡትን ተወዳዳሪዎች ሰነድና ማስረጃዎችን አግባብነት የመጀመሪያ ደረጃ ማጣሪያ በማድረግ ለሚቋቋመው ሀገር አቀፍ ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ያቀርባል፣
5. የሀገር አቀፍ ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት ዕጩ የምርጦች ምርጥ ተሸላሚዎችን በመምረጥ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የበላይ አመራር በማቅረብ ያፀድቃል፣
6. የፀደቁ የምርምርና የፈጠራ ውጤቶች በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ ይደረጋሉ፡፡

## ክፍል ሶስት

## ለተወዳዳሪዎች የሚሰጥ ሽልማት፣ የሽልማት አስተዳደርና የክትትል ስርዓት

### 9. ለተወዳዳሪዎች የሚሰጥ ሽልማት

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በሀገር አቀፍ ደረጃ አሸናፊ ለሆኑ አሰልጣኞችና ሰልጣኞች፡-

1. የዕውቅና ሰርተፊኬት፣
2. ሜዳሊያና፣
3. የገንዘብ ማበረታቻዎች ይሰጣሉ፣
4. ከተሸላሚዎች ፈጠራ ስራ መካከል ችግር ፈቺ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በማወዳደር በሚዘጋጁ ሀገር አቀፍ የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ኤግዚቢሽኖች ላይ ለተጠቃሚዎች እንዲቀርቡ ይደረጋል፣
5. ከተሸላሚዎች መካከል በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የአጭር ጊዜ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎች የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

### 10. የሽልማት አስተዳደርና የክትትል ስርዓት

ሽልማቱን የሚያስተዳድሩትና አፈፃፀሙን የሚከታተሉት ሚኒስቴሩና፣ ኤጀንሲውና የክልልና የከተማ አስተዳደር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲዎች ወይም ኮሚሽን ናቸው፣ በየደረጃው ያሉ የሽልማት አስፈፃሚ አካላት የሽልማቱን አፈፃፀም በየጊዜው ይከታተላሉ፡፡

## ክፍል አራት

## የሽልማት ስርአቱ አካላት ተግባራትና ሀላፊነቶች

### 11. የሚኒስቴሩ ተግባር እና ሀላፊነት፡-

1. በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚደረገው ሽልማት በጀት ያስመድባል፣
2. የበጀት ዓመቱን ሽልማት የጊዜ ሰሌዳ በማውጣት ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች ዕጩ ተወዳዳሪዎችን መርጠው እንዲልኩ ያሳውቃል፣
3. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፌዴራል መ/ቤቶችን ያስተባብራል፣
4. በየደረጃው የሚካሄደውን የሽልማት አፈጻጸም ክትትል ያደርጋል፣

5. በየሽልማት ምድቡ የሚቀርቡ የተወዳዳሪዎችን መረጃ በማደራጀት የመጀመሪያ መረጣ በማድረግ ለሀገር አቀፍ ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ቀጣይ ስራዎች ዝግጁ ያደርጋል፡
6. የተወዳዳሪዎችንና ተሸላሚዎችን መረጃ ያደራጃል፡
7. የላቀ ውጤት ላስመዘገቡት የምርጦች ምርጥ ተሸላሚዎች የማበረታቻ ሽልማት ይሰጣል፡
8. ውጤታማ የሆኑ ፈጠራዎችንና ምርምሮችን ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፡
9. ለተሸላሚዎችም የስራ ፈጠራና የአቅም ግንባታ የአጭር ጊዜ ስልጠና እና የገበያ ትስስር የሚፈጠርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

## 12. ሀገር አቀፍ የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት፡-

1. በሁሉም የሽልማት ምድቦች የቀረቡ ተወዳዳሪዎችን ሰነድ እና ውጤት ትክክለኛነት ያረጋግጣሉ፣
2. በተወዳዳሪዎች የቀረቡ የፈጠራና የምርምር ስራዎችን በጥልቀት በማየት በተሰጠው መስፈርት ይገመግማሉ፤ የማለፊያ ነጥብ በማስቀመጥ ለሽልማት ብቁ የሆኑትን በደረጃ ለይተው ያቀርባሉ፣
3. በተወዳዳሪዎች የተሰሩ ስራዎችን በመስፈርቶቹ መሰረት በመገምገም በሀገር አቀፍ ደረጃ ውጤት ይሰጣሉ፣
4. የተመረጡትን እጩ ተሸላሚዎችን ጠቅላላ የአመራረጥ ሂደትና ውጤት ሪፖርት ለሚኒስቴሩ የበላይ አመራር በማቅረብ ያፀድቃሉ፡፡

## 13. የክልልና ከተማ መስተዳድር ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ ተግባር እና ሀላፊነት፤

1. ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲዎች ወይም ኮሚሽኖች፣ ከሴቶችና ህጻናት ቢሮ እና የሚመለከታቸው አጋርና ባለድርሻ አካላትን ያካተተ የገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ያቋቁማል፡
2. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች በመመሪያው መሰረት ዕጩ ተወዳዳሪዎችን መርጠው ለኤጀንሲው እንዲልኩ ያስተባብራል፣
3. የክልል መስተዳደሮችና ከተማ አስተዳደር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲዎች ወይም ኮሚሽኖች ለሀገር አቀፍ ሽልማት ዕጩ ተወዳዳሪዎችን

መርጠው ከመላካቸው በፊት በራሳቸው በጀት ብቁ መምህራንና ተማሪዎችን አወዳድረው እንዲሸልሙ ድጋፍና ማበረታቻ ያደርጋል፣

4. በየሽልማት ምድቡ የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ እጩ ተሸላሚዎችን ከኮሚቴው ቃለ ጉባኤ እና ከሌሎች ከድጋፍ ሰጪ መረጃዎች ጋር አያይዞ ለሀገር አቀፍ የምርጦች ምርጥ ሽልማት ለሚኒስቴሩ ይልካል፡፡

## 14. የቅሬታ አፈታት ስርዓት

ተወዳዳሪዎችና ተሸላሚዎች ወይም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በሽልማት አመራረጥ ሂደት፤ የተለያዩ አገልግሎቶች እና አሰራሮች ላይ ቅሬታ ካላቸው፣ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥነ-ስርዓት መሰረት የሚፈታ ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 15. የተሻሩ ህጎች

ሀገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሽልማት መመሪያ" ቁጥር 8/2007 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 16. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መመሪያውን ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 17. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

መጋቢት ..... ቀን 2008 ዓ.ም

አብይ አህመድ

ሚኒስቴር

አብይ አህመድ
ሚኒስትር

አባሪ 1

## ሀ. <u>የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የአሰልጣኞች የሽልማት መስፈርት</u>

የአሰልጣኞች የሽልማት የፈጠራ ስራ/ዎች የሚገመገሙት ከታች በተገለፁት መስፈርቶች ይሆናል፡፡

| ተ.ቁ | ክብደት ከ100% | መስፈርት | የሚሰጠው ነጥብ መጠን | በግምገማ ያገኘው ውጤት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 50% | ከእሴት ሰንሰለት ትንተና በመነሳት ችግር ፈች ቴክኖሎጂን በመረዳት ወይም በመበተንና በመገጣጠም ወይም በማሻሻል ወይም በመቅዳት፣ የተዘጋጁ ፕሮቶታይፖች/ቴክኖሎጂዎች ወይም የተሻሻሉ የአሠራር ሂደቶች ብዛት[1] | | |
| | | • ሶስትና ከዚያ በላይ | * እስከ 50% | ____% |
| | | • ሁለት | እስከ 45% | |
| | | • አንድ | እስከ 40% | |
| 2 | 18% | ተፈላጊ ቴክኖሎጂን ለይቶ፣ አዋጭነቱን አውቶ፣ ንድፉንና ናሙናውን በመስራት ወይም በመፈተሽ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ያሸጋገረ | | ____% |
| | | • የቴክኖሎጂ አብገር አንቀሳቃሾችን ያበቃና ቴክኖሎጂን ያሸጋገረ | እስከ 18% | |
| | | • ሊሸጋገሩ የሚችሉ አዋጭ ቴክኖሎጂዎችን የለየና ያቀረበ | እስከ 14% | |
| | | • የእሴት ሰንሰለት ትንተና ብቻ የሰራ | እስከ 10% | |
| 3 | 5% | በሞጁል ካሪኩለምና በማስተማሪያ፣በማሰልጠኛና በመማሪያ ማቴሪያሎች /በTTLM/ ዝግጅት ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ ያደረገና ጥቅም ላይ ያዋለ | | ____% |
| | | • ከሶስት በላይ ማቴሪያሎች | እስከ 5% | |
| | | • ሶስት ማቴሪያሎች | እስከ 4% | |
| | | • ሁለት ማቴሪያሎች | እስከ 3% | |

[1] ለዚህ መስፈርት ነጥብ ሲሰጥ፡

የፈጠራ ፕሮቶታይፖች ወይም ቴክኖሎጂዎች አሰራር ክብደት እና የተሰራው ስራ ችግር ፈችነት ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል፡፡ በፈጠራ ሞጁል/ ናሙና ለውድድር የሚቀርቡ ስራዎች መረጃ በፎቶ ወይም በተንቀሳቃሽ ምስል /በሲዲ/ ወይም በሰነድ የተደገፉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

* እስከ የሚለው ነጥብ አሰጣጥ ከ0% ጀምሮ እስከተጠቀሰው ፐርሰንት መስጠት እንደሚቻል ማሳያ ነው፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | • አንድ ማቴሪያል | እስከ 2% | |
| 4 | 10% | በአካባቢው ለሚገኙ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በቴክኖሎጂ ሽግግርና ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ላይ ድጋፍ በማድረግ አስመዝና ያበቃ | | ____% |
| | | • ከአምስት ኢንተርፕራይዞች በላይ | እስከ 5% | |
| | | • ከ3-5 ኢንተርፕራይዞች | እስከ 3% | |
| | | • ከሶስት ኢንተርፕራይዞች በታች | እስከ 2% | |
| 5 | 5% | ስልጠና በትብብር እንዲካሄድ በማድረግ ኢንዱስትሪዎች እና ተቋማትን ያስተሳሰረ | | ____% |
| | | • ኢንዱስትሪዎችን በመለየት ስልጠናን በጋራ ለመስጠት የመግባቢያ ሰነድ እንዲፈረም ያደረገ እና ስልጠናውን የሰጠና የተከታተለ | እስከ 5% | |
| | | • ኢንዱስትሪዎችን በመለየት ስልጠናን በጋራ ለመስጠት የመግባቢያ ሰነድ እንዲፈረም ያደረገ | እስከ 3% | |
| | | • የትብብር ስልጠና የሚሰጥባቸውን ኢንዱስትሪዎችን የለየ | እስከ 2% | |
| 6 | 5% | ከስራ ባልደረቦች ጋር በመተባበር የተቋሙን አሰልጣኞችንና ሰልጣኞችን ለቴክኖሎጂ አሰራር ማብቃት | | ____% |
| | | • በእያንዳዱ ሁለት የአንድ ለአምስት አደረጃጀት ያበቃ | እስከ 5% | |
| | | • በእያንዳዱ ደረጃ አንድ የአንድ ለአምስት አደረጃጀት ያበቃ | እስከ 3% | |
| 7 | 4% | በቴክኒክና ሙያ ስርዓተ ትምህርት ዝግጅትና የጉድኝት ማዕከላትን በማሻሻል ሥራ ላይ ያለው ተሳትፎ | | ____% |
| | | • ከፍተኛ አስተዋፅኦ | እስከ 4% | |
| | | • መካከለኛ አስተዋፅኦ | እስከ 3% | |
| 8 | 4% | አሠልጣኙ ባለፈው አንድ አመት ያገኘው አማካይ የሥራ አፈፃፀም ውጤት | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | • ከ 4.5 እስከ 5.0 | እስከ 4% | ____% |
| | | • ከ 3.5 እስከ 4.4 | እስከ 3% | |
| | | • ከ 2.5 እስከ 3.4 | እስከ 2% | |
| 9 | 4% | የአሰልጣኙ ባህርይ፣ ስነ ምግባርና ለተቋሙ ንብረት ያለው የባለቤትነት ስሜት | | ____% |
| | | • እጅግ በጣም ጥሩ | እስከ 4% | |
| | | • በጣም ጥሩ | እስከ 3% | |
| | | • ጥሩ | እስከ 2% | |
| | 100% | ከ100% ጠቅላላ ያገኘው ውጤት | | ____% |

* እስከ የሚለው ነጥብ አሰጣጥ ከ 0% ጀምሮ እስከተጠቀሰው ፐርሰንት መስጠት እንደሚቻል ማሳያ ነው።

## ለ. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሰልጣኞች የሽልማት መስፈርት

የሰልጣኞች የሽልማት የፈጠራ ስራ/ዎች የሚገመገሙት ከታች በተገለፁት መስፈርቶች ይሆናል።

| ተ.ቁ | ክብደት ከ100% | መስፈርት | የሚሰጠው ነጥብ መጠን | በግምገማው ያገኘው ውጤት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 50% | ቴክኖሎጂን በመቅዳት ወይም በማላመድ የተሰሩ ችግር ፈች ኘሮቶታይፖች/ ቴክኖሎጂዎች ብዛት[2] | | ____% |
| | | • ሶስትና እና ከዚያ በላይ የቴክኖሎጂ ናሙና ያዘጋጀ | * እስከ 50% | |
| | | • ሁለት ችግር ፈቺ የቴክኖሎጂ ናሙና ያዘጋጀ | እስከ 45% | |
| | | • አንድ ችግር ፈቺ የቴክኖሎጂ ናሙና ያዘጋጀ | እስከ 42% | |
| 2 | 15% | • በውድድሩ ወቅት በተቋሙ በተደረገው የምዘና ሂደት የላቀ ብቃት ያሳየ | እስከ 35% | ____% |
| | | • ከተመዘነው የብቃት ስብስብ በአንድ ዙር በሁሉም ምዘና ብቁ የሆነ | እስከ 15% | |
| | | • በአንድ ዙር በአንድ የትምህርት አሀድ (unit of competency) ብቻ ብቁ ያልሆነ | እስከ 10% | |
| | | • በአንድ ዙር በሁለት የትምህርት አሀድ (unit of competency) ብቻ ብቁ ያልሆነ | እስከ 5% | |
| 3 | 10% | ሰልጣኙ በትብብር ስልጠና በተሳተፈበት ኢንዱስትሪ/ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ በምርትና አሰራር ላይ ያለው አስተዋፅኦ | | ____% |
| | | • ከፍተኛ | እስከ 10% | |
| | | • መካከለኛ | እስከ 8% | |
| | | • አጥጋቢ | እስከ 6% | |
| 4 | 10% | በአንድ ለአምስት አደረጃጀት ዕውቀትና ክህሎቱን ለአባላቱ በማካፈልና በመደገፍ ያበቃ | | |
| | | • በጣም ከፍተኛ | እስከ 10% | |

[2] ለዚህ መስፈርት ነጥብ ሲሰጥ የፈጠራ ኘሮቶታይፖች ወይም ቴክኖሎጂዎች አሰራር ክብደትእና የተሰራው ስራ ችግር ፈችነት ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል። በፈጠራ ሞዴል/ ናሙና ለውድድር የሚቀርቡ ስራዎች መረጃ በፎቶ ወይም በተንቀሳቃሽ ምስል/በሲዲ / ወይም በሰነድ የተደገፉ መሆን ይኖርባቸዋል።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | • ከፍተኛ | እስከ 8% | ______% |
| | | • መካከለኛ | እስከ 6% | |
| 5 | 10% | የሰልጣኙ ባህሪይ፣ ስነ-ምግባርና ለተቋሙ ንብረት ያለው የባለቤትነት ስሜት | | ______% |
| | | • እጅግ በጣም ጥሩ | እስከ 10% | |
| | | • በጣም ጥሩ | እስከ 8% | |
| | | • ጥሩ | እስከ 6% | |
| 6 | 5% | ሰልጣኙ ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረገ ኢኖቫቲቭ ኢንተርፕራይዝ ለመፍጠር በመደራጀት ያደረገው ጥረት | | ______% |
| | | • ተደራጅቶ የቆጠበ | እስከ 5% | |
| | | • የተደራጀ | እስከ 3% | |
| | 100% | ከ100% ጠቅላላ ያገኘው ውጤት | | ______% |

* እስከ የሚለው ነጥብ አሰጣጥ ከ0% ጀምሮ እስከተጠቀሰው ፐርሰንት መስጠት እንደሚቻል ማሳያ ነው።